ሚድሮክ ኢትዮጵያ
ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ቢሮ (ሲኢኦ)

CIT - BULLETIN 7

በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ቢሮ ሥር በተቋቋመው
የኤች አይ ቪ/ኤድስ ኮርፖሬት ኢንተርቬንሽን ቡድን (Corporate Intervention Team on HIV/AIDS)
ተዘጋጅቶ ለሠራተኞችና ለቤተሰባቸው ስለ ወረርሽኙ ግንዛቤ ለማስጨበጥ የቀረበ

«የሰው ልጅ የነፃነትን ጥቅም የሚያውቀው
በጠላት እጅ ወድቆ ግፍ ሲፈጸምበት ሲሆን
የጤንነትንም ጥቅም ይበልጥ የሚረዳው ታሞ ሲተኛ ነው፡፡»

# እውነተኛ ታሪክ

## ትግል፤ በህይወት ለመኖር ሰሚ ጆሮ እንፈልጋለን!

አንድ ፈላስፋ ስለሕይወት በሚያስረዳበት ወቅት «መልካሙን ሕይወት ለማግኘት የምንችለው (በመልካም ህይወት ለመርካት የምንችለው) አሁን ባለን ነገር መደሰት ስንችልና አሁን የሌለንን ነገር ዛሬ ካለን ነገር የተሻለ አድርገን በመገመት እሱኑ ለማግኘት መመኘት ስናቆም ነው፡፡ በደስታ መኖር የምንችለው ዛሬ ባለን ነገር መርካት ስንችል ብቻ ነው፡፡ አስደሳችና አስደናቂ የሆነችዋ የዛሬ ሕይወታችንን ስቃይዋንና አበሳዋን የምናሳያት በነገው ህልም ላይ ዋዥቀንና ተንጠልጥለን ዛሬን ማጣጣም ሲያቅተን ነው፡፡» በማለት ገልጾ ነበር፡፡

ውድ አንባቢያን፤ እንኳን ለአዲሱ ዓመት ለ1997 ዓ.ም በሰላም፣ በጤና አደረሳችሁ እያልኩኝ ስለ ሕይወት ይህን ያህል ካልኩኝ እውነተኛ የታሪክ ተሞክሮዬን እንደሚከተለው አቀርብላችኋለሁ፡፡ ዕድሜዬ በጎልማሳዎቹ አካባቢ ውስጥ የምገኝ ሰው አድርጎኛል፡፡

ዕድሜዬ ለሥራ እንደደረሰ በ1974 ዓ.ም. ለ22 ዓመታት ያህል እስካሁን ድረስ ባገለገልሁበት ድርጅት ውስጥ ተቀጠርሁ፡፡ በድርጅቱ ማለትም በአሁኑ ጊዜ ዘመናዊ የህንፃ ኢንዱስትሪ (MBI) በመባል የሚታወቀው ኩባንያ ዛሬም ሠራተኛ ነኝ፡፡ በድርጅቱ ውስጥ ያለኝን ታሪክ በአጭሩ እዚህ ላይ ልግታና ወደ ዋናው ዓላማዬ ስገባ በአሁኑ ወቅት ዓለምን በተለይም አፍሪካን ይልቁንም ደግሞ ኢትዮጵያን የመሳሰሉትን ሀገሮች ከድህነት ጋር ተዳምሮ በተለይም አምራቹን ዜጋ በመፈታተን በከፍተኛ ደረጃ በማጥቃት ላይ ያለውንና መድኃኒት የለሹን ኤች አይ ቪ/ኤድስን በሚመለከት የራሴን ተሞክሮ ለማቅረብ እወዳለሁ፡፡

እኔ ከቫይረሱ ጋር የምኖር ወገን ስሆን ቫይረሱ በደሜ ውስጥ መኖሩን በትክክል በምርመራ ካወቅሁ 7 ዓመታት ይህል አስቆጥሬያለሁ፡፡ ምርመራውን ያደረግሁት የትዳር ጓደኛዬ ከዚህ ዓለም በሞት ከተለየችኝ ከ5 ዓመት በኋላ ሲሆን በአጠቃላይ ቢያንስ ለ12 ዓመታት ያህል ከቫይረሱ ጋር ኖሬያለሁ ማለት ነው፡፡

ቫይረሱ በደሜ ውስጥ መኖሩ ሲነገረኝ እጅግ ተስፋ በመቁረጥ መጠጣት፣ ማጨስ፣ መቃም፣ ወዘተ. የመሳሰሉት ጎጂ ድርጊቶች የዕለት-ተዕለት ተግባሮቼ ሆኑ፡፡ በዚያን ጊዜ ማለትም ከ12 ዓመታት በፊት እንዳሁኑ የምክር አገልግሎት እጅግም የማይሰማበትና ያልተስፋፋበት ዘመን በመሆኑ ተስፋ በመቁረጥ በነጋታው ከዚህ ዓለም የምለይ ሰው አድርጌ ራሴን ቆጠርኩኝ፡፡ ጊዜው እየተራዘመ ሲሄድ እግዚአብሔር ብርታቱን ሰጥቶኝ የመጣውን ሁሉ በጸጋ ከመቀበልና እራሴን ከማበረታታት በስተቀር ምንም አማራጭ እንደሌለኝ የግድ ብረዳም በዚህ ድርጅት ውስጥ እየሠራሁኝ አልፎ አልፎ ጭንቀትና እራስን ማግለል እንዲሁም ጤናማ አለመሆን ልዩ ምልክቶቼ ሆነው መታየት ጀመሩ፡፡ ይህንን ችግሬን ለማቃለል የነበረኝ ብቸኛ አማራጭ በወቅቱ የድርጅቱ ሥራ አስኪያጅ ለነበሩት የግል ምሥጢሬን ማወያየት (መንገር) ያለብኝ መሆኑን በማመን አዕምሮዬ ዕረፍት ነሳኝ፡፡ በዚህም ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ ይህን ችግሬን በመግለጽ ከሥራ አስኪያጃችን ጋር ባደረግሁት ውይይት የመኖር ተስፋ እንዳለኝና ከራሳቸው ጀምሮ ሌላው ሠራተኛም ቢሆን ስለራሱ ምንም እንደማያውቅ ይልቁንም እኔ ራሴን ያወቅሁ በመሆኔ ከዚህ በኋላ ልረበሽና አዕምሮዬን ዕረፍት ልነሣው እንደማይገባ በቂ ምክርና ግንዛቤ ለማግኘት ቻልኩ፡፡ የኩባንያችን ሥራ አስኪያጅ «አይዞህ የተቻለውን ሁሉ እንረዳሀለን!» በማለትና ምሥጢሬን በመያዝ ከቲዎሪ ባሻገር ኢኮኖሚያዊ እገዛ ያደረጉልኝ ሲሆን እስከ ዛሬ ድረስ በሕይወት ለመኖር እንድችል የሕይወት ብርሃኔ ለመሆን መብቃታቸውን አስታውሳለሁ፡፡

ኤች አይ ቪ/ኤድስን በኔ ተሞክሮ ሙሉ በሙሉ ለመግለጽ አስቸጋሪ ቢሆንም ከቫይረሱ ጋር አብሬ እየኖርኩ በመሆኑ መልዕክቴን በአጭሩ እንደሚከተለው አስተላልፋለሁ፡፡

ኤች አይ ቪ/ኤድስን እንደ ክፉ ጎረቤት (ደባል) እቆጥረዋለሁ፡፡ ክፉ ጎረቤት ቢሆንም ከጠበቁትና ካልተዘናጉለት ሊያጠቃ አይችልም፡፡ በአንድ ጣሪያ ሥር አብረው የሚኖሩት ከሆነ ደግሞ ከዚህ ለየት ያለ ነው፡፡ ከደባልነት ወጥቶ ለመኖር ሌላ ምርጫ ከሌለ ግን ያለው ዕድል ተከባብሮ መኖር ስለሚሆን የማይፈለገውን ነገር መተው የግድ ነው፡፡ በቃ ዝም ብሎ ሳይዘናጉና ጥንቃቄን ሳያጎድሉ ተስማምቶ መኖር ነው! በቃ!!በቃ!!

ከላይ ለመግለጽ እንደሞከርኩት ኤች አይ ቪ ፖዘቲቭ መሆኔን ካወቅኩኝ ጀምሮ በተለይም ከቫይረሱ ጋር ለዓመታት መኖሬን በሚገባ ማጤንና ስለሁኔታውም ረጋ ብዬ ማስተዋል ከጀመርኩበት ጊዜ አንስቶ በወቅቱና በአስቸኳይ መወገድ የሚገባቸውን በደባልነት የተያዙ አጉል ልማዶችን ሁሉ አስወግጄ ከቫይረሱ ጋር ተስማምቼ ለመኖር ወሰንኩ፡፡ የራሴን መድኃኒት በራስ ጥረት ማዘጋጀት እንደነበረብኝም ስለተረዳሁኝ ከአልኮል፣ ከሲጋራ፣ ከብስጩነት፣ እራስን ከማግለል ነፃ በማድረግ የመኖር ራዕይ ይዤ በመጓዝ ሕይወቴን መምራት ተያይዤ እነሆ እስከዛሬም በጥንካሬ እየተራመድሁ ነው፡፡ እኔ በዚህ አኗኗር ላይ እያለሁኝ በሹክሹክታም ይሁን በተለያየ መንገድ ስለኔ የተረዱ የሥራ ባልደረቦቼ የበሽታውን ስም መጥራት በመፍራትም ይሁን «ማወቃችንን ብንገልጽለት ይከፋዋል» በማለትም ይሁን አላውቅም ብቻ እንዲሁ «አይዞህ! በርታ! ሕክምናህን ተከታተል!» እያሉ በግል አስተያየት የሚሰጡኝ ሠራተኞች እየተበራከቱ መጡ፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰርና በቢሯቸው ሥር የተቋቋመው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ኮርፖሬት ኢንተርቬንሽን ቡድን ባደረጓቸው የተለያዩ ጥረቶች በመበረታታት ቢያንስ ለመሥሪያ ቤቴ ሠራተኞች እራሴን ግልጽ ለማድረግ ወሰንኩኝ፡፡ በነገራችን ላይ እንደ MBI ሠራተኞችና የሥራ ኃላፊዎች ስለበሽታው በቂ ግንዛቤ

ኖሯዋቸውና በበሽታው ለተያዙ ወገኖችም የላቀ ፍቅር የሚያሳዩ በርካታ ኢትዮጵያውያን በየቦታው ቢኖሩ ኖሮ ማግለልና መድሎ ባንድ ሌሊት ይጠፉ እንደነበር ምስክርነቴን መግለጽ እወዳለሁ::

ወደ ዋናው ሃሳቤ ልመለስና በቀጥታ ከሠራተኛው ባገኘሁት ፍቅር የተነሳ በተዋረድ ከቅርብ አለቃዬ ጀምሮ ለአንድ አንድ ኃላፊዎች እራሴን ግልጽ በማድረግ ሲያመኝ እረፍት እንዳደርግና የሥራ ጫና እንዳይበዛብኝ በመተባበር የሥራ ባልደረቦቼ የኔን ሥራ በመሸፈን ከፍተኛ ትብብር ይደረግልኝ ጀመር:: በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር በዶ/ር አረጋ ይርዳው በወጡትና ኤች አይ ቪ/ኤድስን በሚመለከቱት የሥራ መመሪያዎች በመታገዝ ይህ የሠራተኛው ፍቅር ጭራሽ የሚገፋፋ ኃይል ሊሆንልኝ በመቻሉ በሲ.ኢ.ኦ. ቢሮ በሚመራው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ኮርፖሬት ኢንተርቬንሽን ቡድን አመራር ሥር በድርጅቱ በሚካሄደው ወርሃዊ የትምህርት ፕሮግራም አማካኝነት መድረክ ላይ ወጥቼ እራሴን በይፋ በማስተዋወቅ እነሆ ማስተማር ጀምሬያለሁ::

ታዲያ ለዚሁ ለዕድሜዬ መራዘምና ብሎም እስከማስተማር የደረስኩት በድርጅቱ ሠራተኞችና ሠራተኛ ማኅበር እንዲሁም በማኔጅመንቱ ልዩ ልዩ ድጋፍ መነሻ መሆኑን እየገለጽኩኝ እውነቴን ነው የምላችሁ ይህችን መፅሔት ለምታነቡ ሁሉ እራሳችሁን ተመርምራችሁ ያወቃችሁም ሆናችሁ ያላወቃችሁም አንድ ቀን ሰፋ ባለ መድረክ በአካል ተገናኝተን እንማማራለን የሚል መልካም ሃሣቤን ላካፍላችሁ እወዳለሁ:: ከመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በሚደረገው የባህርይ ለውጥ የማምጣት ትምህርትና ጥረት በመጠኑ ለውጥ ያለ ቢሆንም ገና ይቀራል እያልኩኝ በዚህ በአዲሱ ዓመት እያንዳንዱ ሠራተኛ ተመርምሮ እራሱን ማወቁ ብልህነት ነው በማለት አስተያየቴን በመስጠት በሌላ ጊዜ ዕድሉን ካገኘሁ በዚሁ መጽሔት በመጣጥፍ ልንገናኝ እንችላለን በማለት እሰናበታችኋለሁ:: አመሰግናለሁ!!

# ሌላኛው ዕውነታ!

በሀገራችን ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ያለው ዕውቀትና የበርካታ ሰዎች ግንዛቤ እያደገና እየጨመረ ቢመጣም የቫይረሱ ሥርጭት ግን እየቀነሰ ሲሄድ አይስተዋልም:: ከቶ ይህ ለምን ይሆናል?! በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ቢሮ ሥር የተዋቀረው የኤች አይ ቪ/ኤድስ ኢንተርቬንሽን ቡድን (ሲ.አይ.ቲ.) ከተመሠረተበት ጊዜ አንስቶ እያከናወነ ያለው ተግባር የዚህን ቫይረስ ሥርጭት ለመግታት መወሰድ በሚገባቸው የመከላከል እርምጃዎች ላይ ያተኮረ ነው:: በተለይም በአንድ በኩል ለሥርጭቱ 85-87% ተጠያቂ የሆነውን ጥንቃቄ የጎደለው የግብረ-ሥጋ ግንኙነትን አደገኛነት ባለማቋረጥ በማስተማርና በሌላ በኩል ደግሞ የሚደረጉት ማናቸውም የዕውቀትና የግንዛቤ ማሳደጊያ ጥረቶች ሠራተኞቻችንን በተናጠል ብቻ ሳይሆን ቤተሰቦቻችንንም ጭምር የሚያካትት መሆን እንዳለበት በማስመልከት ላይ የተመሠረተ ነው::

ሀገራዊ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የቫይረሱን ሥርጭት ለመግታት የሚደረጉት ጥረቶችና የመከላከል እርምጃዎች አደጋ ሊያንዣብብባቸው የቻለው ስለቫይረሱ ዕውቀት ያለውና ግንዛቤውንም ያዳበረው የኅብረተሰብ ክፍል በዚያው መጠን እያደገ የሚሄድ የባህርይ ለውጥ ለማሳየት ባለመቻሉ ነው:: በመሆኑም ይህንን ዐቢይ ችግር ዘወትር ልናጤነው ይገባል:: በተለያዩ አካባቢዎች የምንገኝ ሁሉ ለሕይወታችን አስጊ የሆነን ነገር የመዳፈር ልምዳችንን ማስወገድ ይኖርብናል:: የተለያዩ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና ኤኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በሽፋንነት በመጠቀም ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ ካለን ዕውቀትና ግንዛቤ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ የባህሪይ ለውጥ ለማምጣት አለመቻላችን በመጪው ትውልድ ዘንድ ሲያስወቅስ የሚኖር መጥፎ ድርጊት ነው::

ከላይ እንደተጠቀሰው በሀገራችን የተደረጉት ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ስለ ኤች አይ ቪ/ኤድስ እያደገ የመጣው ዕውቀትና እየዳበረ ያለው ግንዛቤ አደገኛ በሆነና ጥንቃቄ በጎደለው ልቅ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ልምድ ላይ ተጽዕኖ አሳድሮ ማስለወጥ አልቻለም:: በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች የተወሰነ አደገኛ ሁኔታን ለመለማመድ ፈቃደኛ በመሆን ሞትን የመረጡ ይመስላሉ ማለት ይቻላል::

በዚህ ጥያቄ ዙሪያ እያንዳንዳችን የየዕለት ኑሯችንንና ልምዳችንን በሚገባ ልናጤን ያስፈልገናል:: ኤች አይ ቪ/ኤድስን በሚመለከት 2% (ሁለት በመቶ) አደገኛነት ያለበት ድርጊት እንኳን ቢሆን አደጋ በሌለበት 98% ከመዝናናት ይልቅ ሞትን ስለሚያስከትለው 2% መጨነቅ ብልህነት ነው:: ብዙ ሰዎች የራሳቸውን ዕውቀትና እምነት በመፍጠርና በመከተል የኤች አይ ቪ ቫይረስ ሥርጭትን ለመግታት የሚደረገውን ጥረት ሲያደናቅፉ ይስተዋላሉ:: ስለዚህም ጥንቃቄ የጎደለውና ለአደጋ የሚያጋልጥ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ማዘውተር፣ ሌሎች ቫይረሱ በሚተላለፍባቸው መንገዶች ላይ መወሰድ የሚገባውን ጥንቃቄ በቸልተኝነት ማለፍ፣ እንዲሁም ወደሞት የሚያመራ እንኳን ቢሆን በተወሰነ ደረጃ አደጋን በድፍረት የመጋፈጥ ልምድ አለማስወገድ ወዘተ ዛሬ ለምንመለከተው የኤች አይ ቪ ቫይረስ ሥርጭት አለመገታት ምቹ ሁኔታዎችን እየፈጠሩ ናቸው::

በአሁኑ ወቅት በሚድሮክ ኢትዮጵያ ቺፍ ኤግዚኪዩቲቭ ኦፊሰር ቢሮና በሥሩም በሚተዳደሩት ኩባንያዎች ውስጥ እየተካሄደ ያለው ግንዛቤን የማሳደግና ዕውቀትን የማስጨበጥ ተግባር አንድ እርምጃ ወደፊት መራመድ ያለበት እርከን ላይ እየደረሰ ነው:: በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ምርመራና ራስን የማወቅ ሒደት ከወትሮው በተሻለ እየተከናወነ ቢሆንም ውጤቱን በመግለጽ ከቫይረሱ ጋር አብረው የሚኖሩ መሆናቸውን በይፋ የሚያሳውቁ ግን እጅግ በጣም አነስተኛ ናቸው:: ለዚህ በዋነኛነት እንደ ምክንያት ሆኖ የሚጠቀሰው «አድልዎና መገለል» ሲሆን ይህንን ለመቋቋም ቆርጠው የሚነሱ ሲገኙ ደግሞ ባልደረቦቻችን ተገቢውን እንክብካቤ ለማድረግ ሠራተኞቻችን ይበልጥ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል::

በዚህ የመጽሔታችን ዕትም ታሪኩን በመጠኑ የገለጸልን ባልደረባችን ለብዙዎቻችን አርአያነቱ የሚያጠያይቅ አይደለም:: ወቅታዊ ተግባራችን የቫይረሱን ሥርጭት ለመከላከል ከምናካሂደው የግንዛቤ ማሳደጊያ ጥረት ጎን ለጎን እያንዳንዱን ግለሰብ የሚያውቀውን ምን ያህል በተግባር እየተረጎመ መሆኑን በማበረታታትና ከቤተሰቡ ጋር እየወሰደ ያለውን የጋራ እርምጃ በማገዝ ላይ ማተኮር ይኖርብናል:: ሰዎች የሚያውቁትን በተግባር እንዲተረጉሙ እንርዳቸው!!